## ትምህርት አራት

**►እግዚአብሔር አብርሃምን ለምን ለይቶ ጠራው?**

ይህንን ጥያቄ ከመመለሳችን በፊት ጥሪ ወይም መጠራት ማለት ምን ማለት ነው የሚለውን እናስቀድም። እግዚአብሔር ሁሉንም ሰው ወደ ልጁ የሠርግ ግብዣ ይጠራል(ማቴ 22፡ 3-9)፤ ይህም ማለት እግዚአብሔር ኃጢአተኞችን በወንጌል በኩል ለደኅንነት ይጠራል(ኢሳ 55፡ 1፣ ዮሐ 3, 16፣ ሐዋ 12፡ 30)። የወንጌሉን ጥሪ ግን ሁሉም አይቀበሉም፤ የሚቀበሉት በልቡናቸው ልዩ የእግዚአብሔር ጥሪ ሲሰማቸው ብቻ ነው(ማቴ 13፡ 9፣ 22, 14፣ ዮሐ 6፡ 44)። የዚህ ዓይነቱ ጥሪ የንስሓ ጥሪ በመባል ይታወቃል(ሉቃ 5፡ 32፣ ማር 2፡ 17 ማቴ 9፡ 13)። ይህ ጥሪ ለነፃነትና ከክርስቶስ ጋር ኅብረት እንዲኖረን ነው(1 ቆሮ 1፡ 9፣ ገላ 5፡ 13)።

በሌላ በኩል ደግሞ እግዚአብሔር አንድን ግለ ሰው ብቻ ለይቶ ለተለየ አገልግሎት ይጠራል። ለምሳሌ አብርሃም፣ ሙሴ እና ነቢያቶች መጥቀስ ይቻላል። ይህ የተጠራው ሰው ሙሉ የሆነ ነፃነት ስላለው ጥሪውን የመቀበል ወይም ያለመቀበል መብት አለው። ጥሪውን ከተቀበለ እግዚአብሔር ለዚህ ሰው አንድ ልዩ የሆነ ተልእኮ ይሰጠዋል። በዚህ በጎ ፈቃደኛ በሆነው ሰው አማካኝነትም እግዚአብሔር ሕዝቡን እንዲገለገል ያደርጋል። የአብርሃምም ጥሪ ከዚህ ጋር የተያያዘ ነው። በአጠቃላይ አብርሃም የተጠራበት ምክንያት ከዘሩ ክርስቶስ በሥጋ እንዲወለድ ነው። “የምድር ነገዶች በአንተ ይባረካሉ”(ዘፍ 12፡ 2-3) የሚለው ተስፋ የተፈጸመው በክርስቶስ ነው።

**►አብርሃም ማለት ምን ማለት ነው? እግዚአብሔር ምን ያህል ጊዜና በምን ምክንያትስ አነጋገረው?**

አብርሃም የመጀመሪያ ስሙ አብራም ነበር፤ አብራም ማለት ታላቅ አባት ማለት ነው። በኋላ ግን እግዚአብሔር ለብዙ አሕዛብ አባት ትሆናለህ በማለት አብርሃም ብሎ ስሙን ለወጠ(ዘፍ 17፡ 1-5)። አብርሃም የታራ ታላቅ ልጅ ነው። እግዚአብሔር አብረሃምን ብዙ ጊዜ በተለያዩ ጉዳዮች ወይም ምክንያቶች አነጋገረው። ከእነዚህም ውስጥ ለመጥቀስ ያህል፦

1) ለእስራኤልሕዝብአባቶችየመጀመሪያውይሆንዘንድከትውልድአገሩከከለዳውያንዑርእንዲወጣበጠራውጊዜአነጋገረው(ዘፍ 12፡ 1-6 እናሐዋ 7፡ 2-3)።

2) ከአባቱከታራናከአጐቱልጅከሎጥጋርሆኖከዑርተነሥቶወደካራንሄደ። ከካራንወጥቶወደከነዓንምድርሲገባያችንምድርለዘሩእንደሚሰጥበግልጥአነጋገረው (ዘፍ 12፡ 7)።

3) ለጥቂትጊዜበሴኬም፣በቤቴልናበአዜብ ወይም በደቡብ አገር ቆይቶ በራብ ምክንያት ወደ ግብጽ ተጓዘ። ከዚያም ተመልሶ በኬብሮን ከቆየ በኋላ ከሎጥ በተለያየ ጊዜ አነጋረው(ዘፍ 13)።

4) ወራሽልጅእንደሌለውአይቶባዘነጊዜበራእይአነጋገረው(ዘፍ 15፡ 1-21)።

5) ስሙንአብርሃምብሎበለወጠጊዜተገልጦአነጋገረው(ዘፍ 17)።

6) በመምሬየአድባርዛፍሥርተገልጦካነጋገረውበኋላወደቤቱገብቶሚስቱሣራልጅ እንደምትወልድለት ተስፋውን ነገረው። በኋላም ስለ ሰዶምና ገሞራ ብዙ ጊዜ ከእግዚአብሔር ጋር ተወያየ(ዘፍ 18)።

7) ልጁንይስሐቅንእንዲሠዋበፈተነውጊዜአነጋግሮታል(ዘፍ 22፡ 1-18)።

**► የአብርሃም የትዳር ሕይወት ምን ይመስል ነበር? ስንት ልጆችስ ነበሩት? የሕይወቱ መጨረሻስ እንዴት ተጠናቀቀ?**

አብርሃምእግዚአብሔርየሰጠውንተስፋሳይጠብቅአጋርከተባለችግብጻዊት ገረዱ እስማኤልን ወለደ(ዘፍ 16)፤ እግዚአብሔር ቃል ኪዳኑንና ምልክት የሆነውን ግዝረት ከሰጠው በኋላ ግን የተስፋ ልጁ ይስሐቅ ከሚስቱ ከሣራ ተወለደለት(ዘፍ 17 እና 21, 1-3)። ሚስቱ ሣራ ከሞተች በኋላ ቀጡራ የተባለችውን ሴት አግብቶ 6 ልጆች ወለደ(ዘፍ 25፡ 1-2)።

አብርሃም በከነዓን አገር በድንኳን ውስጥ ይኖር ነበር። ባረፈበትም ሁሉ መሠዊያን ይሠራ ነበር። ዘሩ አገሩን እንደሚወርስ ተተነበየለት። ተስፋውም በምድራዊ ርስት ብቻ ሳይሆን በሰማያዊ አገርም እንደሚፈጸም ተረዳ(ዕብ 11፡ 8-16)። በ175 ዓመቱ ሞተና በኬብሮን ተቀበረ (ዘፍ 25፡ 9-10)።

**► አብርሃም ስለ ሰዶምና ገሞራ ሕዝቦችእግዚአብሔርንእንደማለደ (እንደለመነ) ይታወቃል፤ የሰዶምናገሞራሕዝቦችኃጢአትምንነበር? እግዚአብሔርስለምንሊያጠፋቸውወሰነ?**

ሰዶምና ገሞራ የሚባሉት መንደሮች በዮርዳኖስ ሸለቆ የተቈረቈሩ ከተሞች ነበሩ። ኃጢአታቸው በተለይም የዝሙት ሥራቸው አስጸያፊ ስለነበር እግዚአብሔር ሊያጠፋቸው ወሰነ (ዘፍ 18፡ 20፣ 19፡ 5-9)። ሁለት መላእክት ሎጥን ከከተማው ካወጡ በኋላ እግዚአብሔር ሰዶምንና ገሞራን በእሳትና በዲን አጠፋ(ዘፍ 19፡ 10-26)። ሰዶምና ገሞራ አሁን በጨው ባሕር እንደተሸፈኑ ይገመታል። ሰዶም የክፋት ሁሉ የፍርድም ምሳሌ በመሆን ተጠቅሷል(ኢሳ 1፡ 9-10፣ ኤር 23፡ 14፣ ሕዝ 16፡ 46፣ ማቴ 10፡ 15፣ ራእ 11፡ 8)።

ይህጥፋትከመድረሱበፊትግንአብርሃምስለነዚህከተሞችእግዚአብሔርንተማጽኖታል። የአብርሃምጥያቄወይንምጭንቀትየነበረውከተማውውስጥየሚገኙትንንጹሓንሰዎችእንዴትከኃጢአተኞችጋርአብረውይደመሰሳሉየሚልነበር።እንዲህምአለው“በእርግጥ በደል የሌለባቸውን ሰዎች ከኃጢአተኞች ጋር ታጠፋለህን? በከተማዪቱ ውስጥ ኀምሳ ደጋግ ሰዎች ቢገኙ ከተማዪቱን በሙሉ ትደመስሳለህን? ስለ ኀምሳው ደጋግ ሰዎች ስትል ከተማዪቱ እንዳትጠፋ አታደርግምን? በደል ያልሠሩት ደጋግ ሰዎች ከኃጢአተኞች ጋር ታጠፋለህ ብዬ አላስብም፤ ይህንን እንደማታደርገው አምናለሁ፤ ይህንንማ ካደረግህ ደጋግ ሰዎች ከኃጢአተኞች ጋር መቀጣታቸው ነው፤ ይህ ከቶ አይሆንም! የዓለም ፈራጅ በትክክል መፍረድ ይገባው የለምን?” በማለት እግዚአብሔርን ጠየቀ። እግዚአብሔርም ዐሥር ንጹሓን ሰዎች እንኳ ከተማዪቱ ውስጥ ቢገኙ ከተማዪቱን እንደማይደመስስ ቢነግረውም ከተማዪቱ ከመደምሰስ አላመለጠችም፤ በእርግጥም ሁሉም በኃጢአት ተዘፍቀው ነበርና ።

**► ሰዶማውያን ማለት ምን ማለት ነው? ከሰዶም ከተማ ጋር ምን የሚያዛምደው ነገር አለን?**

ሰዶማውያንማለትግብረ ሰዶምን የሚፈጽሙ ማለት ነው። ግብረ ሰዶም የሚፈጽሙ ማለት ደግሞ ወንድ ከወንድ ጋር ሴት ከሴት ጋር ዝሙት የሚያደርጉ ማለት ነው። ይህ ኃጢአት በሰዶም ይበዛ ነበርና ግብረ ሰዶም ተባለ(ዘፍ 19፡ 5)። በሙሴ ሕግ ይህን ኃጢአት የሚፈጽሙ ሁሉ ያለ ምሕረት ይገደሉ ነበር(ዘሌ 20፡ 13፣ ዘዳ 23፡ 17)። ሆኖም ይህ ኃጢአት በእስራኤል የተለመደ ነበር(መሳ 19, 22፣ 1ነገ 14፡ 24፣ 2ነገ 23፡ 7)። ሰዎች እግዚአብሔርን

መፍራትና ማምለክ ሲተዉ ለጣኦታትም ሲሰግዱ የዚህ ዓይነት መጥፎ መንፈስ ያድርባቸዋል፤ በአሕዛብ መካከል ይህ ኃጢአት ይገኛል(ሮሜ 1፡ 22-27፣ 1ጢሞ 1፡ 9-11)፡፡ ይህ ዓይነት መንፈስ ያደረባቸው ሰዎች በወንጌል ኃይል ሊድኑ ይችላሉ(ማር 6፡ 11፣ 1ቆሮ 6፡ 9-11)፡፡

**► የሰዶምና የገሞራ ሕዝቦች ብዙ ብዙ ኃጢአት በመፈጸማቸው ምክንያት እግዚአብሔርን አሳዝነው እንደነበና እግዚአብሔርም እንደቀጣቸው ከላይ ተገልጿል፤ እንደ ቅዱሳን መጻሕፍትአገላለጽሌሎችከባድቅጣትሊያስከትሉየሚችሉኃጢአቶችየትኞቹናቸው?**

በእስራኤልሕግነፍስየገደለ፣ወላጆቹንየመታወይምየሰደበ፣ሰንበትንየሻረ፣ ባዕድአምልኮትንየተከተለ፣ያመነዘረ፣ ከተፈጥሮጋርየማይስማማየጾታግኙኝነትንያደረገየሞትቅጣትይፈረድበትነበር(ዘጸ 21፡ 12-17፣ 22፡ 18-20፣ዘሌ 24፡ 14-16፣ዘኁ 15፡ 32-36)፡፡

ሰውሰውንቢጎዳእንደጉዳቱመጠንካሣመክፈልነበረበት(ዘጸ 21፡ 23 - 25,30)፡፡ ሰው ሲያጠፋ ሊገረፍ ይችላል፤ የግርፋቱ ቁጥር ግን እንደ ኃጢአቱ መጠን ሆኖ ግርፋቱ ግን በአርባ የተወሰነ ነበር(ዘዳ 25፡ 1-3)፡፡ በእስራኤል ዘንድ የሞት ቅጣት በድንጋይ በመውገር፣ በእንጨት ላይ በመስቀል(ዘዳ 21፡ 22-23፣ ዘዳ 22፡ 24)፣ በሮማውያ ዘንድ ራስን በመቁረጥ (ማቴ 14፡ 10) ወይም በስቅላት ይፈጸም ነበር(ማር 15፡ 21-25)፡፡

በአዲስ ኪዳን ስናይ ደግሞ ከቅጣት ጋር በተያያዘ መልኩ የተጠቀሱ ነገሮች አሉ፡፡ እግዚአብሔር ሰውን እንደ ሥራው ይቀጣል(ሉቃ 12፡ 46-48፣ ራእ 20፡ 11-15)፡፡ በደለኛ ለዘለዓለም ይቀጣል(ዳን 12፡ 2፣ ማቴ 25፡ 46)፡፡ እግዚአብሔር ልጆቹን ይቀጣል፤ ይህ ለጥቅማቸው ስለሆነ በትዕግሥት ሊቀበሉት ይገባል(ዕብ 12፡ 5-11)፡፡

**► አብርሃም በአዲስ ኪዳን ውስጥ በብዙ ቦታዎች በጥሩ ተምሳሌትነቱ ተጠቅሶ ይገኛል፤ የእምነት አባት በመባልም ይታወቃል፤ ይህ ሊያሰኘው የቻለው ምንድን ነው?**

አብርሃም ጥሩ ተምሳሌትነቱና የእምነት አባትነቱ በተደጋጋሚ ከተጠቀሱበት ምክንያቶች ውስጥ የሚከተሉትን ይገኙበታል፤

1) ለእግዚአብሔርታዛዥሆኖበመገኘቱ (ዮሐ 8፡ 39-40፣ዕብ 11፡ 17-19፣ያዕ 2፡ 21-24) ምሳሌነቱበተደጋገሚይጠቀሳል፡፡ የአብርሃምታዛዥነትየሚወደውንአንድልጁንይስሐቅንለእግዚአብሔርመሥዋዕትአድርጎእስከማቅረብይደርሳል(ዘፍ 22)፡፡

2) እምነቱጠንካራስለነበርናጽድቅሆኖስለተቆጠረለትየምእመናንሁሉአባትተብሎተጠራስለዚህበእርሱየማመንምሳሌበክርስቶስየሚያምኑ ሁሉ በእምነት እንደሚጸድቁ ተደጋግሞ ተነግሯል(ሮሜ 4 እና ገላ 3፡ 6-7)፡፡

3) በጠንካራውእምነቱየዓለምወገኖችሁሉበእምነትየአብረሃምእውነተኞችልጆችየተስፋውምወራሾችተብለውበመጠራታቸውምክንያትአብረሃምተደጋግሞይጠቀሳል (ሮሜ 4፡ 11-12፣ሮሜ 9፡ 7-8 ገላ 3፡ 7-9 እናቁ. 29) ፡፡

**► አብረሃም ከልጆቹ መካከል ለየትኛው ነው እግዚአብሔር "የአብርሃምን ተስፋ" ያጸናለትና የባረከውም?**

እግዚአብሔር የአብርሃምን ተስፋ ያጸናለትና የባረከውም ለልጁ ለይስሐቅ ነው (ዘፍ 26, 3-5፣ ዘፍ 26፡ 12-29)፡፡ ይስሐቅ ማለት "ይስቃል" ማለት ነው፡፡ ከላይ እንደተገለጸው

የአብርሃምና የሣራ ልጅ ሲሆን የያዕቆብም አባት ነው። ሣራ በስተእርጅናዋ ወለደችው(ዘፍ 17፡ 15-21፣ ዘፍ 18፡ 9-15 እና ዘፍ 21፡ 1-7)። ከመወለዱ 25 ዓመት ቀደም ብሎ ለአብርሃም የተሰጠው የዘር ተስፋ በይስሐቅ ሊፈጸም ጀመረ(ዘፍ 12፡ 1-3፣ ማቴ 1፡ 2 ገላ 3፡ 16)።

ይስሐቅ ተገረዘ (ዘፍ 21፡ 4)። "በይስሐቅ ዘር ይጠራልሃል" ስለተባለ እስማኤል ተሰደደ (ዘፍ 21, 8-14)። አብርሃም ይስሐቅን ለመሥዋዕትነት አቀረበ(ዘፍ 22)። ይስሐቅ ርብቃን አገባ (ዘፍ 24)። ከጸለየም በኋላም ዔሳውንና ያዕቆብን ወለደችለት(ዘፍ 25፡ 19-26)።

**በዘመኑ ራብ በሆነ ጊዜ ወደ ፍልስጤም ተሰደደ፤ እግዚአብሔርም ወደ ግብጽ አትውረድ አለው(ዘፍ 26፡ 1-2)። 180 ዓመት ሲሆነው ሞተ(ዘፍ 35፡ 28-29)። ጳውሎስ በእምነት የተወለዱትን የእግዚአብሔር ልጆች "የተስፋ ቃል ልጅ" በሆነው በይስሐቅ መሰላቸው(ሮሜ 9፡ 6-9፣ ገላ 4፡ 21-31)።**

**► ይስሐቅንና ሚስቱ ርብቃ በሕይወታቸው ሁሉ ሲያዝኑበት የኖረው ጉዳይ ምን ነበር?**

ከልጆቻቸውመካከልበኩርየነበረውናብኩርናውንለታናሽወንድሙለያዕቆብበቀይምስርወጥየሸጠውዔሳውከወገኖቹውጭከሆኑትሁለትሴቶችጋርጋብቻበመፈጸሙነው (ዘፍ 26፡ 34-35)። ይስሐቅያዕቆብንእንደመረቀውናሚስትእንዲፈልግወደመስጴጦምያእንደላከውዔሳውተረዳ፤ ይስሐቅያዕቆብንሲመርቀው "ከነዓናዊት ሴት እንዳታገባ" ብሎ ያዘዘው መሆኑን ሰማ፤ በዚህም አባቱ ይስሐቅ የከነዓናውያንን ሴቶች እንደማይወድ ዔሳው ተገነዘበ፤ ስለዚህ ከዚህ በፊት ካገባቸው ሌላ በተጨማሪ ወደ አብርሃም ልጅ ወደ እስማኤል ሄዶ ልጁን ማሕላትን አገባ፤ እርስዋም የነባዮት እኅት ናት።

**► በተለምዶ በኩር የሆነ ልጅ የአባቱ ምርቃት እንደሚቀበል ከመጽሐፍ ቅዱስ እንረዳለን፤ ታድያ ይስሐቅ የበኩር ልጁ ዔሳው እያለ ለምንድን ነው ለያዕቆብ የባረከው?**

በእርግጥይስሐቅባሕሉንወይምየተለመደውንአደራረግበመከተልየበኩርልጁንዔሳውንሊመርቀውይፈልግነበር፤ ነገርግንያዕቆብበእናቱበርብቃምክርታግዞአርጅቶናዐይኖቹታውሮየነበረውንአባቱንበማታለልምርቃቱንተቀበለ።አባቱምያዕቆብንእንዲህበማለትመረቀው፦"እግዚአብሔርከሰማይየሚያረሰርስጠልይስጥህ፤ ምድርህንያለምልምልህ፤ እህልህንና የወይን ጠጅህን ያብዛልህ፤ መንግሥታት ይገዙልህ፤ ሕዝቦችም ያገልግሉህ፤ በወንድሞችህ ሁሉ ላይ አለቃ ሁን፤ የእናትህንም ልጆች ይስገዱልህ፤ የሚረግሙህ የተረገሙ ይሁኑ፤ የሚመርቁህ የተመረቁ ይሁኑ"(ዘፍ 27፡ 28-29)።

**► አባቱን ይስሐቅን በማታለል ምርቃት(በረከትን) የተቀበለው ያዕቆብ የሕይወት ጉዞ ምን ይመስል ነበር?**

- ያዕቆብ ማለት "ተረከዝን ይይዛል" ማለት ነው። ይህም መንትያ ከነበረው ወንድሙ ከዔሳው ጋር ሲወለድ የዔሳውን ተረከዝ ይዞ ከእናቱ ማሕፀን በመውጣቱ ነው ያዕቆብ ሊባል የቻለው (ዘፍ 25፡ 19-26)። ስለዚህ ያዕቆብ ርብቃ ለይስሐቅ ከወለደችለት መንታዎች ታናሹ የዐሥራ ሁለቱ የእስራኤል ሕዝብ ነገዶች አባት ነው።

- ያዕቆብ ከዔሳው ለማምለጥና ሚስት ለማግኘት ወደ እናቱ ወንድም ወደ ላባ ሄደ(ዘፍ 27፡ 42 - 28, 9)። የመሰላልን ሕልም አየ፤ የአብርሃምም ተስፋ ተሰጠው(ዘፍ 28፡ 10-22)።

- ያዕቆብ ሃያ ዓመት ላባን አገልግሎ ልያንና ራሔልን አገባ፤ ብዙ ልጆችም ወለደ፤ ብዙ ከብትም አገኘ(ዘፍ 29-30)።

- እግዚአብሔር ወደ ከነዓን እንዲመለስ ባዘዘው ጊዜ ከላባ ቁጣ(ዘፍ 32-33) ጠበቀው፡፡ እግዚአብሔር በጵኒኤል(ዘፍ 32፡ 22-32) በቤቴልም (ዘፍ 35፡ 9-15) ተገለጠለት፤ ስሙንም እስራኤል ብሎ ጠራው፡፡

- ብዙ ዓመት በከነዓን ከኖረ በኋላ(ዘፍ 33፡ 18-45) በረሃብ ጊዜ ወደ ግብጽ ሄደ(ዘፍ 46-47)፡፡ ትንቢት እየተናገረ የዮሴፍን ልጆች የራሱንም ዐሥራ ሁለት ልጆች ከባረከ በኋላ 147 ዓመት ሲሆነው ሞተ(ዘፍ 47፡ 27-49, 33)፤ በአብርሃምም መቃብር ተቀበረ(ዘፍ 50)፡፡ ከእርሱ የተገኘው ሕዝብ እስራኤል አንዳንዴም "ያዕቆብ" ይባላል(ዘኍ 23፡ 10 ኢሳ 41፡ 8-21)፡፡

- ያዕቆብ ዐሥራ ሁለት ወንዶች ልጆች ነበሩት፤ እነዚህም የልያ ልጆች የያዕቆብ የመጀመሪያ ልጅ ሮቤል፣ ስምዖን፣ ሌዊ፣ ይሁዳ፣ ይሳኮርና ዛብሎን ናቸው፡፡ የራሔል ልጆች ዮሴፍና ብንያም ናቸው ፡፡ የራሔል አገልጋይ የነበረችው የባላ ልጆች ዳንና ንፍታሌም ናቸው፡፡ የልያ አገልጋይ የነበረችው የዚልፋ ልጆች ጋድና አሴር ናቸው ፡፡

**► ከያዕቆብ ዐሥራ ሁለቱ ልጆች ውስጥ የትኛውን ነው በአባቱ በጣም የተወደደውን የተባረከው?**

- በአባቱ የተወደደውና የተባረከው የያዕቆብ ዐሥራ አንደኛው ወንድ ልጅ የነበረውና የራሔልም በኵር ልጅ ዮሴፍ ነው፡፡ ዮሴፍ ማለት "ይጨምር" የሚል ትርጉም ይሰጣል(ዘፍ 30፡ 22-24)፡፡ ከጸባዩ መልካምነትና ከዝናው፣ ከፈጸመውም ታላቅ ሥራ የተነሣ ከያዕቆብ ልጆች ሁሉ የተከበረ ሆነ፡፡ አባቱ በተለይ ወደደው፡፡ ብዙ ሕልም ስላየና ስለ ወንድሞቹ መጥፎ ወሬ ለአባታቸው ስላወራ ጠልተው ሸጡት (ዘፍ 37)፡፡

- በግብጽ ባርያ ሆኖ ሳለ በጶጢፋር ቤት ለአስተዳዳሪነት ተሾመ፡፡ የጶጢፋር ሚስት በሐሰት ስትከሰው ግን በግዞት ታሰረ፡፡ እዚያም ሞገስን አግኝቶ ከግዞት ቤት አለቃ በታች ኀላፊ ሆነ (ዘፍ 39)፡፡ ሕልሞችን ለመተርጐም ስለቻለ ፈርዖን ፈታው፤ በአገሩም ሁሉ ላይ አለቃ አደረገው (ዘፍ 40, 41)፡፡ ሰባት ዓመት እህልን እየሰበሰበ በረሀብ ዘመን ብዙ ሰዎችን የገዛ ራሱን ቤተሰብ ጭምር ከሞት አዳነ(ዘፍ 42-45)፡፡

- ዮሴፍ ግብጻዊቷን አሰናትን አግብቶ ምናሴንና ኤፍሬምን ወለደ(ዘፍ 41፡ 50-52)፡፡ አባቱንና ወንድሞቹን ወደ ግብጽ አስመጥቶ መገባቸው(ዘፍ 46፡ 1-47)፡፡ አባቱ በከነዓን ቀበረው(ዘፍ 49፡ 29-50) ፡፡ ዮሴፍ በወንድሞቹ ቂም አልያዘም(ዘፍ 50፡ 15-21)፡፡ ሳይሞት ዐፅሙን በከነዓን እንዲቀብሩት የእስራኤልን ልጆች በማማሉ እምነቱን ገለጠ(ዘፍ 50፡ 22-24፣ ኢያ 24፡ 32፣ ዕብ 11፡ 22)፡፡

- ዮሴፍ ከእስራኤል ነገዶች የሁለቱ አባት ሆነ፡፡ ያዕቆብ ብኵርናው ለዮሴፍ ይሁን በማለት የዮሴፍን ልጆች ምናሴንና ኤፍሬምን ባረከ፤ በስሞቻቸውም ነገደ ምናሴና ነገደ ኤፍሬም ተብለው ተጠሩ(1 ዜና መ. 5፡ 1 ዘፍ 48 ዘኍ 1፡ 4-10፣ ዘዳ 33፡ 13-17)፡፡

**► እስራኤላውያን በግብጽ አገር በባርነት ለብዙ ዘመናት እንደኖሩ ይታወቃል፤ ለመሆኑ እስራኤላውያን ከታሪኩ መጀመሪያ እንዴት ግብጽ ውስጥ ሊገኙ ቻሉ? የእስራኤላውያን የግብጽ ኑሮ አጀማመር እንዴት ነው?**

- ዮሴፍ በወንድሞቹ ተሸጦ ወደ ግብጽ ከወረደ በኋላ ግብጻዊቷን አስናትን አግብቶ ምናሴንና ኤፍሬምን እንደወለደና ዘሩም እዛው ግብጽ ውስጥ እንደበዛ ይታወቃል፡፡ በሌላ መልኩ ደግሞ ዮሴፍ በግብጽ ውስጥ አስተዳዳሪ በሆነበት ዘመን በግብጽና በሌሎችም አገሮች ለሰባት ዓመታት ከባድ ረሃብ ሆነ፤ ዮሴፍ ግን ቀድሞ በጐተራዎች እህል አከማችቶ ስለነበር ግብጻውያን አልተራቡም፡፡ በግብጽ እህል መኖሩን የሰማው ያዕቆብ እሱና ልጆቹ በረሃብ ከመሞታቸው

በፊት ልጆቹን ከነበሩበት ከከነዓን ወደ ግብጽ እንዲሄዱ ያደርጋቸዋል(ዘፍ 42፡ 1-2)፡፡ በመጨረሻም ያዕቆብና ቤተሰቡ በግብጽ አገር በዮሴፍ ጥበቃ ሥር መኖር ጀመሩ፤ እጅግም ተባዙ፡፡ እያንዳንዱ ከቤተሰቡ ጋር ሆኖ ወደ ግብጽ ምድር የገቡት እስራኤል ተብሎ የተጠራው የያዕቀብ ልጆች ብዛት ሰባ ነበሩ(ዘጸ 1፡ 1-6)፡፡ እነዚህ እስራኤላውያን ተዋልደው ቁጥራቸው ከመብዛቱ የተነሣ የግብጽን ምድር ሞሉአት፤ እጅግም ብርቱዎች ሆኑ፡፡

**► እስራኤላውያን ግብጽ ውስጥ በዮሴፍ ጥበቃ ሥር በታላቅ እንክብካቤ ንብረት አፍርተው፣ ቤተሰብ መሥርተውና ተደላድለው ይኖሩ ከነበረ ኑሮአቸው እንዴት ወደ ባርነት ሊለወጥ ቻለ? ግብጻውያን ለምን እስራኤላውያንን መጥላት ጀመሩ?**

- ዋናው የግብጻውያን ጥላቻ መነሻ የሆነው ዮሴፍ ስለሞተና እርሱ ያደረገው መልካም ነገር ሁሉ የማያውቅ አዲስ ንጉሥ በግብጽ አገር ስለተነሣ ነው፡፡ እርሱም ለሕዝቡ እንዲህ አለ “እነሆ እነዚህ እስራኤላውያን ቁጥራቸው በዝቶአል፤ የኀይላቸውም ብርታት አስጊ ሆኖብናል፤ ከዚህም የተነሣ ከጠላቶቻችን ጋር ተባብረው ከወጉን በኋላ ከአገሪቱ አምልጠው መሄድ ይችላሉ፤ ስለዚህ ቁጥራቸው እየበዛ እንዳይሄድ ኑ አንድ ዘዴ እንፍጠርባቸው”(ዘጸ 1፡ 8-10)፡፡ ስለዚህ ንጉሡ በሰላም ተፋቅረውና ተከባብረው ይኖሩ በነበሩት ሁለቱ ሕዝቦች መካከል የጥላቻ መንፈስ ዘራባቸው፡፡
- የግብጽ ንጉሥ ጨካኞች የሆኑ አሠሪዎች ሾመባቸው፤ ርኅራኄ በጎደለውም ጭካኔ በባርነት ያሠሩአቸው ጀመር፤ ጭቃ በማቡካት፣ ጡብ በማዘጋጀትና በእርሻ ውስጥ በጭካኔ ከባድ ሥራ በማሠራት ሕይወታቸው መራራ እንዲሆን አደረጉ፤ ነገር ግን እስራኤላውያን በተጨቁኑ መጠን ቁጥራቸው ይበልጥ እየበዛና በምድሪቱም ላይ እየተስፋፉ ሄዱ፤ ከዚህም የተነሣ ግብጻውያን እስራኤላውያንን ፈሩአቸው(ዘጸ 1፡ 12-14)፡፡
- ከዚህም በላይ ንጉሡ ሁለት ግብጻውያን አዋላጆች ጠርቶ የዕብራውያን (የእስራኤላውያንን) ሴቶች ሲያዋልዱ የሚወለደው ሕፃን ወንድ ከሆነ ወዲያውኑ እንዲገድሉት አዘዘ፡፡ አዋላጆች ግን እግዚአብሔርን ስለ ፈሩ የግብጽ ንጉሥ እንዳዘዛቸው አላደረጉም፤ እንዲያውም ወንዶችም ልጆች በሕይወት እንዲኖሩ አደረጉ፡፡ ከዚህ በኋላ ንጉሡ ከእስራኤላውያን አዲስ የሚወለደውን ወንድ ልጅ ሁሉ እያነሣችሁ ዓባይ ወንዝ ውስጥ ጣሉ ሲል ለሕዝቡ ጥብቅ ትእዛዝ በማስተላልፍ ሕዝቡ ለእስራኤላውያን ያላቸውን ጥላቻ የከፋ እንዲሆን አደረገው፡፡

**የትምህርቱ አዘጋጅ ፦ አባ ምሥራቅ ጥዩ**

**የትምህርቱ አስተባባሪ፦ አቶ ተስፋዬ ባደገ**

የሚከተሉትን ጥያቄዎች ከመለሱ በኂላ ወደ ሀገረስብከቱ የተልእኮ ትምህርት ክፍል ይላኩት፡፡

**ስም --------------------------------- ኮድ-------- ቁምስና-------------------ውጤት-------**

1- እግዚአብሔር አብራምን ለመጀመሪያ ጊዜ ሲጠራው “አገርህን ትተህ ከዘመዶችህና ከአባትህ ቤተሰብ ተለይተህ እኔ ወደማሳይህ አገር ሂድ” ብሎታል፡፡ በዚህ ጊዜ እግዚአብሔር ብዙ ነገሮች ቃል ገብቶለታል(ዘፍ 12፡ 1-3)፡፡ ከሚከተሉት ውስጥ አንዱ እግዚአብሔር ለአብራም ከገባለት ቃል ውስጥ የማይካተተው የትኛውን ነው?

*ሀ) ረዥም ዕድሜ እንድትኖር አደርግሃለሁ፤ ሞትም አይነካህም ለ) ዘርህን አበዛዋለሁ፤ ታላቅ ሕዝብም ይሆናል፤ እባርክሃለሁ ሐ) ስምህንገናናአደርገዋለሁ፤ለሌሎችምበረከትትሆናለህ መ) የሚመርቁህን እመርቃለሁ የሚረግሙህን እረግማቸዋሁ፤ ሠ) በአንተአማካይነትሕዝቦችሁሉይባረካሉ፡፡*

2- አብራም ከዶርላዖሜርና ከእነርሱ ጋር አብረው የነበሩትን ነገሥታት ድል አድርጎ ሲመለስ የልዑል እግዚአብሔር ካህን የነበረው የሳሌም ንጉሥ መልከ ጼዴቅም ለአብራም እንጀራና የወይን ጠጅ አመጣለት፤ ባረከውም፡፡ በዚህ ጊዜ አብራም ለመልከ ጼዴቅ ምን አደረገለት? (ዘፍ 14፡ 17-24)፡፡

*ሀ) በምላሹ አብራም መልከ ጸዴቅን ባረከው፡፡ ለ) መልከ ጼዴቅ ስለ አብራም የወደፊት ኑሮ ትንቢት ተናገረው፡፡ ሐ) አብራም በምርኮ ካገኘው ሀብት ሁሉ አንድ ዐሥረኛውን ለመልከ ጼዴቅ ሰጠው መ) መልከ ጼዴቅ ለአብራም ዐሥራት ሰጠው፡፡*

3- አብራም ስሙ ከተቀየረ በኂላ አብርሃም ተብሎ መጠራቱን ይታወቃል፡፡ ለመሆኑ አብርሃም ለምንድን ነው የእምነት አባት ተብሎ በክርስቲያኖች ዘንድ የሚታወቀው ወይም የሚጠራው?

*ሀ) አገርህን ትተህ ከዘመዶችህና ከአባትህ ቤተ ሰብ ተለይተህ እኔ ወደማሳይህ አገር ሂድ ሲባል በመቀበሉና በተግባር በመፈጸሙ(ዘፍ 11) ለ)ይስሐቅን እንዲሠዋለት ባዛዘው መሠረት የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ስላከናወነ (ዘፍ 22)፡፡ ሐ) አብረሃም ቢሸመግልም ልጅ እንደሚወልድ ከእግዚአብሔር የተሰጠውን የተስፋውን ቃል አምኖ በመቀበሉ(ዘፍ 18)፡፡ መ) ከእግዚአብሔር ጋር የቀረበ ወዳጅነት ስለነበረውና በእምነቱም ብርቱና ጻድቅ ስለነበር(ዘፍ 18፡ 17) ሠ) ሁሉም*

4- ከሚከተሉት ውስጥ ሰዶማውያንን ወይም ከሰዶማውያን ከሚለው ቃልና ትርጓሜ ጋር የማይካተተው የትኛው ነው?

*ሀ) ሰዶማውያን ማለት ግብረ ሰዶምን ማለትም ወንድ ከወንድ ጋር ፣ ሴት ከሴት ጋር ዝሙት የሚያደርጉ ማለት ነው፡፡ ለ) ግብረ ሰዶማዊነት በተፈጥሮ የሚመጣ በሽታ ወይም በተፈጥሮ የሚሰጥ ባሕሪይ ነው፡፡ ሐ) በሙሴ ሕግ ይህን ኃጢአት የሚፈጽሙ ሁሉ ያለ ምሕረት ይገደሉ ነበር፡፡ መ) ሰዎች እግዚአብሔርን መፍራትና ማምለክ ሲተዉ ለጣኦታትም ሲሰግዱ የዚህ ዓይነት መጥፎ መንፈስ ያድርባቸዋል፡፡ ሠ) ግብረ ሰዶማውያን ከተለወጡ በወንጌል ኃይል ሊድኑ ይችላሉ፡፡*

5- ሰዎች ጋብቻ በሚፈጽሙበት ጊዜ ሙሽሮቹን “ጋብቻችሁን የአብርሃምና የሣራ ጋብቻ ይሁን ” ወይም“ጋብቻችሁእንደአብርሃምናእንደሣራየተባረከይሁን”እያሉበተለያየመልኩከአብርሃምናከሣራ ጋርእያዛመዱሲመርቁይሰማል፡፡
ለመሆኑለምንድንነው“ጋብቻችሁእንደአብርሃምናእንደሣራይሁን”የሚባለው፡፡

## የትምህርት አራት ምላሾች

1. ሀ
2. ሐ
3. ሠ
4. ለ
5. - ልጅ ባይወልዱም በትዳራቸው እስከመጨረሻው ጸንተው ስለኖሩ።
    - ሣራ ልጅ መውለድ ባትችልም አብርሃም ሳያንቋሽሻትና ሳያዋርዳት በፍቅርና በክብር ስለያዛት።
    - በትዳራቸው ውስጥ ፈሪሐ እግዚአብሔር ስለነበር፤
    - እግዚአብሔር ስለባረካቸውና ዘራቸውን ስላበዛላቸው፤
    - ሌላም… ሌላም ሊሆን ይችላል።